# በኢትዮጵያ የአበባ አምራች ድርጅቶች ለ30ሺ ዜጎች ሥራ ማስገኘታቸውን ሚኒስቴሩ አስታወቀ

ጅማ (ኢዜአ)፡- የኢትዮጵያ የአበባ አምራች ድርጅቶች ከ30ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች ሥራ ማስገኘታቸውን የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ ከዘርፉ በ2001 በጀት ዓመት 306 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘትም ታቅዷል፡፡

የሚኒስቴሩ የአበባ ልማት አማካሪ ዶክተር አድሃኖም ነጋሲ ሰሞኑን በጅማ ከተማ በተካሄደ ዓውደ ጥናት ላይ እንደ ተናገሩት በሀገሪቱ በመስፋፋት ላይ የሚገኙት 81 ድርጅቶች 70 በመቶ ሴቶችን ያካተተ የሰው ኃይል በልማቱ በማሰማራት ከፍተኛ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እየሰጡ ናቸው፡፡

ከድርጅቶቹ 94 በመቶ የሚሆኑት በኦሮሚያ ክልል ቀሪዎቹ ደግሞ በደቡብ ክልል እንደሚገኙ ጠቅሰው፤ በልማቱም የየአካባቢዎቹን ነዋሪዎች በመቅጠር ገቢ የሚያገኙበት ሥራ መፍጠራቸውን አስረድተዋል፡፡

ከእነዚህ 32ቱ በኢትዮጵያውያን፣ 44ቱ በውጭና ቀሪዎቹ በውጭና በኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች የተቋቋሙት ድርጅቶች ለሠራተኞቻቸውና በድርጅቶች አቅራቢያ ለሚኖር ሕዝብ የንጹህ መጠጥ ውሃ፣ የኤሌክትሪክ፣ የትምህርትና የጤና አገልግሎት በመስጠት ተጠቃሚ ማድረጋቸውንም አማካሪው አብራርተዋል፡፡

ልማቱን በተጨማሪ ክልሎች ለማስፋፋት በአማራ ክልል ባህር ዳር ከተማ አካባቢ 700 ሄክታር መሬት በመልማት ላይ እንደሚገኝና በትግራይ ክልልም ለማስጀመር ዝግጅት እየተደረገ ነው ብለዋል፡፡

ድርጅቶቹ በ2001 የበጀት ዓመት ልማቱን ወደ 1ሺ480 ሄክታር መሬት በማሳደግ 206 ሚሊዮን ዶላር ለማግኘት መታቀዱንም ዶክተር አድሃኖም አስታውቀዋል፡፡

ኢትዮጵያ በተጠናቀቀው የበጀት ዓመት 1ሺ ሄክታር መሬት በማልማት 111 ሚሊዮን ዶላር ማግኘቷንም አማካሪው አስታውሰዋል፡፡